# የት/ቤት መልእክት መላኪያ

## አዲስ አውቶሜትድ የመልእክት መላኪያ ሥርዓት

## ፈጣን እውነታዎ

- **አጭር የጽሑፍ መልእክቶች የሚላኩበት ከስልክ ቁጥር** 675-87 ነው። ባለፉት ጊዚያት በትምህርት ቤት መልእክት መላኪያ ይደርስዎት ከነበር፣ እንደተመሰገበ እውቂያ (ኮንታክት) ሊወጣ ወይም ሊያሳይዎ ይችላል።
- የመገናኛ ዘዴ እና የቋንቋዎች ምርጫዎችዎን ጨምሮ **በኢንፊኒት ካምፓስ** (IC) **ውስጥ ባሉዎት ምርጫዎች መሠረት መልእክቶች የሚደርሱዎት ይሆናል።**
- **ምርጫዎችዎን በ**DPS **የወላጅ እና የተማሪ ፖርታሎች ውስጥ ያስተካክሉ።**



DPS በትምህርት ቤት አንዳች ድንገተኛ ነገር በሚኖር ጊዜ ለቤተሰቦች የሚያሳውቅበት አዲስ ሥርዓትን ለመጠቀም በመጀመር ላይ ነው። የትምህርት ቤት መልእክት መላኪያ መሣሪያችን (SchoolMessenger) የድንገተኛ መልእክቶችን ለወላጆች እና ለአሳዳጊዎች እንዲሁም ለመቀበል ለፈረሙ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ለመላክ ከኖቬምበር አጋማሽ ጀምሮ መጠቀም እንጀምራል። እነዚህ መልእቶች የሚያካትቱት፡-

- ከትምህርት ቤት መዘጋት፣ ቅድሚያ መለቀቅ ወይም ዘግይቶ መጀመር ጋር የሚገናኙ የጽሑፍ፣ የኢሜል እና የስልክ መልእክቶችን፣ እና
- ስለ ከህንጻ ውስጥ አለመውጣት (ሎክዳውን) ወይም በሮችን መቆለፍ፣ መብራት ማጥፋትና መደበቅን (ሎክአውት) መልእክቶችን ይሆናል።

**የትምህርት ቤት መልእክት መላኪያ መሣሪያው በኢንፊኒት ካምፓስ** (IC) **ውስጥ ባሉዎት ምርጫዎችዎ መሠረት የአጭር የጽሑፍ፣ የስልክ ወይም የኢሜል ሊሆን የምችል የእንኳን ደህና መጡ መልእክትን ኖቬምበር አጋማሽ ውስጥ ይጠብቁ።** DPS ወደፊት ለሚኖሩት ትምህርት ቤት ተኮር መረጃ ልውውጦች ሙሉ በሙሉ ወደ የት/ቤት መልእክት መላኪያ መሣሪያ እስከሚዛወር ድረስ ትምህርት ቤቶች የኢንፊኒት ካምፓስን (IC) መልእክት መላኪያን መጠቀማቸውን ይቀጥላሉ።

**ጥያቄዎች አሉዎ ወይስ ተጨማሪ መረጃ ይፈልጋሉ?**
www.dpsk12.org/schoolmessenger ን ይጎብኙ።